# ለተቀባዮች እና ለእንክብካቤ አቅራቢዎች የሚሆን  የእውነታ ወረቀት

## ዕድሜያቸው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ግለሰቦች የኮሮናቫይረስ በሽታ 2019 (COVID-19) ን ለመከላከል የ Moderna COVID-19 ክትባት የድንገተኛ አጠቃቀም ፈቃድ (EUA)

በ SARS-CoV-2 የተፈጠረውን የኮሮናቫይረስ 2019 (COVID-19) በሽታ ለመከላከል የ Modern COVID-19 ክትባት ቀርቦሎታል ። ይህ የእውነታ ወረቀት በአሁኑ ጊዜ የ COVID-19 ወረርሽኝ በመኖሩ ምክንያት የሚወስዱትን የ Moderna COVID-19 ክትባት ጉዳቶች እና ጥቅሞችን መረዳት እንዲችሉ የሚረዳን መረጃ የያዘ ነው፡፡

የ Moderna COVID-19 ክትባት COVID-19 ን እንዳያገኙ  የሚከላከል ክትባት ነው፡፡  COVID-19 ን ለመከላከል የአሜሪካ የምግብ እና የመድኃኒት አስተዳደር (FDA) ያጸደቀው ክትባት አይደለም ፡፡

ስለ Moderna COVID-19 ክትባት መረጃ ለማግኘት ይህንን የእውነታ ወረቀት ያንብቡ። ጥያቄዎች ካሉዎት የክትባት አቅራቢውን ያነጋግሩ ፡፡ Moderna COVID-19 ን ክትባት መውሰድ የእርስዎ ምርጫ ነው

ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት በሁለት ዶዝ በአንድ ወር ልዩነት በጡንቻ ላይ ይሰጣል፡፡

ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት ሁሉንም ሰዉ ለይጠቅም ይችላል፡፡

ይህ የመረጃ ወረቀት ልሻሻል ስለሚችል ቀጥሎ ያለዉን ድረገጽ ይጎብኙ
www.modernatx.com/covid19vaccine-eua.

**ይህን ክትባት ከመዉሰዱዎ በፍት መታወቅ የምገባቸዉ ነገሮች፡**

### COVID -19 ምንድን ነው?

የ COVID-19 በሽታ SARS-CoV-2 ተብሎ በሚጠራው ኮሮናቫይረስ ይከሰታል ፡፡ የዚህ አይነቱ

ኮሮናቫይረስ ከዚህ በፊት አልታየም ፡፡ ቫይረሱ ካለበት ሌላ ሰው ጋር በመገናኘት በ COVID-19 ሊያዙ ይችላሉ ፡፡ እሱም በአብዛኛው ሌሎች አካላትን ሊጎዳ የሚችል የመተንፈሻ አካላት በሽታ ነው ፡፡ በ COVID-19 የተያዙሰዎች ከቀላል ምልክቶች እስከ ከባድ ህመም ድረስ የተለያዩ ምልክቶች እንደሚታዩባቸው ሪፖርት ተደርጓል ፡፡ በቫይረሱ ከተያዙ ከ 2 እስከ 14 ቀናት በኋላ ምልክቶቹ ሊታዩ ይችላሉ ፡፡ ምልክቶቹ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡ ትኩሳት ወይም ብርድ ብርድ ማለት፣ ሳል፣ የትንፋሽ እጥረት፣ ድካም፣ የጡንቻ ወይም የአካል ህመም፣ ራስ ምታት፣ አዲስ የጣእም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት፣ የጉሮሮ መቁሰል፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ፣ ተቅማጥ፡፡

### ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት ምንድነዉ?

Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ያልተረጋገጠ ግን COVID-19 የሚባለዉን በሽታ ይከላከላል ተብሎ የምታሰብ Moderna ክትባት ከ COVID-19 ሊከላከል የሚችል ያልፀደቀ ክትባት ነው። COVID-19 ን ለመከላከል በ FDA የተረጋገጠ ክትባት የለም ፡፡

FDA እድመያቸዉ 18 እና ከዝያ በላይ የሆኑ ሰዎች በ EUA ስር ቶሎ ብለዉ ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት እንድወስዱ ፈቅዶዋል፡፡

ስለ **የድንገተኛ አጠቃቀም ፈቃድ** (**EUA**) EUA መረጃ ለማግኘት በዝህ የመረጃ ወረቀት መጨረሻ ላይ EUA ምንድነዉ? የምለዉ ርዕስ ስለሚያገኙ ያንብቡት፡፡

### ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት ከመዉሰድዎ በፍት ክትባቱን ለምሰጡት መንገር የምገባዎ ነገር ምንድነዉ?

ክትባቱን ለምሰጡት ሰዎች የጤንነቱዎን ሁኔታ ይንገሯቸዉ፡፡ ይህም ከዝህ በታች ያሉትን ያጠቃልላል፡

- አለርጅ ካለቦት
- ትኩሳት ከለቦት
- የደም አለመረጋጋት ካለቦት
- የህክምና ክትትል እያደረገ መሆኑዎን
- እርግዝና ወይም የእርግዝና ዕቅድ መኖሩን
- እያጠቡ መሆኑን
- ሌላ የCOVID-19  ክትባት መዉሰዱዎን

**Moderna COVID-19 የሚባለዉን ክትባት ማን ይወሰወዳል?**
FDA እድመያቸዉ 18 እና ከዝያ በላይ የሆኑ ሰዎች በEUA ስር ቶሎ ብለዉ ይህ Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት እንድወስዱ ፈቅዶዋል፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉን ክትባት እነ ማን አይወስዱም?**
ከዝህ በታች ያሉት ችግሮች ካሉቦት Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት መዉሰድ የለቦትም፡፡

- ከዝህ በፍት የመጀመርያ ዙር ክትባት ስወስዱ አለርጅክ ከሆኑቦት
- በክትባቱ ዉሰጥ ከተጨመሩ ንጥረ ነገሮች ዉስጥ አለርጅክ የምሆኑቦት ነገር ካለ

**Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት ዉሰጥ የተጨመሩ ንጥረ ነገሮች ምንድናቸዉ?**
Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ዉሰጥ የተጨመሩ ንጥረ ነገሮች: messenger ribonucleic acid (mRNA), lipids (SM-102, polyethylene glycol [PEG] 2000 dimyristoyl glycerol [DMG], cholesterol, and 1,2-distearoyl-sn-glycero-3-phosphocholine [DSPC]), tromethamine, tromethamine hydrochloride, acetic acid, sodium acetate, and sucrose የምባሉት ናቸዉ፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት እንደት ይሰጣል?**
Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት በመርፌ በጡንቻ ለይ ይሰጣል፡፡

Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት በአንድ ወር ልዩነት ሁለት ግዜ ይሰጣል፡፡

Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ሙሉ ዶዝ ለማግኘት አንዴ ከወሰዱ በኋላ ከአንድ ወር በኋላ አሁንም ድጋሚ መዉሰድ አለቦት፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ከዝህ በፍት ስራ ላይ ዉሎዋልን?**
ይህ Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ያልተረጋገጠ ነዉ፡፡ በህክምና ሙከራ ላይ እድሜያቸዉ 18 እና ከዝያ በላይ የሆኑ በቁጥር 15,400 የምሆኑ ሰዎች Moderna COVID-19 የሚባለዉን ክትባት ወስደዋል፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት ጥቅሙ ምንድነዉ?**
አሁን በለዉ የህክምና ሙከራ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት በአንድ ወር ልዩነት ሁለቴ ብወሰድ COVID-19 የምባለዉን በሽታ ይከላከላል ተብሎ ይታሰባል፡፡ COVID-19 የምባለዉ በሽታ ቆይታዉ አይታወቅም፡፡

**በዝህ Moderna COVID-19 በተባለዉ ክትባት ሊመጣ የምችል የጎንዮሽ ጉዳት ምንድነዉ?**
በዝህ Moderna COVID-19 በሚባለዉ ክትባት ልመጣ የሚችል ርፖርት የተደረገ የጎንዮሽ ጉዳት፡

- በክትባት ቦታ ላይ የሰዉነት መቆጣት መታየት፡ ዉጋት፣ እብጠት፣ የማቃጠል ስሜት፣ የክትባቱ ቦታ መጠንከር ወይም ቀይ መሆን
- በጠቅላላ የጎንዮሽ ጉዳት፡ የድካም ስሜት፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ ህመም፣ብረድ ብርድ ማለት ፣ ማቅለሽለሽ ፣ ማስታወክ እና ትኩሳት

Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት ከባድ የአለርጅክ ችግር ያመጣል ተብሎም አይታሰብም፡፡ የአለርጅክ ምልክት የምታይብን Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት ወስደን ከተወሰነ ደቅቃ እስከ አንድ ሰአት ነዉ፡፡ ይህንን ለመቆጣጠር ክትባቱን የምሰጡ ሰዎች ከክትባቱ በኋላ የሚመጣዉን ችግር ለመከታተል ዕዛዉ ያቆያሉ፡፡ ከባድ የአለርጅ ችግር መኖሩ የምታወቀዉ

- ትንፋሽ ማጠር
- የፊትና የጉሮሮ ማበጥ
- ቶሎ ቶሎ መተንፈስ
- ሽፍታ
- ድብርትና ድካም

ከዝህ በላይ የተዘረዘሩት የ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት ላይሆን ይችላል፡፡ ከዘህም የባሳ የጎንዮሽ ጉዳት ልያጋጥምም ይችላል፡፡ የ Moderna COVID-19 የምባለዉ ክትባት የጎንዮሽ ጉዳት እስካሁንም እየተጠና ይገኛል፡፡

**ለዝህ የጎንዮሽ ጉዳት ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?**
የአለርጅ ምልክት ከታየቦት 9-1-1 ይደዉሉ፣ወይም በአከባብዎት ያለ ሆስፒታል ይህዱ፡፡

ሀይለኛ የጎንዮሽ ጉዳት ከታየቦትና የማይሄድ ከሆነ፣ ክትባት የምሰጡትን ሰዎች ወይም የጤና ባለሙያ ያግኙ፡፡

የክትባቱን የጎንዮሽ ጉዳት ለ **FDA/CDC Vaccine Adverse Event Reporting System (VAERS)** ርፖርት ያድርጉ፡፡ VAERS ማገኛ ስልክ 1-800-822-7967 ወይም ይህን ድረግጽ ይጎብኙ https://vaers.hhs.gov/reportevent.html. እባኮትን በርፖርት ፎርም ላይ “Moderna COVID-19 Vaccine EUA” የሚለዉን በመጀመሪያዉ መስመር ቁጥር 18 ላይ ይጨምሩ፡፡

በተጨማርም ModernaTX, Inc. at 1-866-MODERNA (1-866-663-3762) ላይ የጎንዮሽ ጉዳት ርፖርት ማድረግ ይችላሉ፡፡

**V-safe** ላይም እንድትመዘገቡ ዕድል ይሰጠዎታል፡፡ **V-safe** በስማርት ሞባይል ለይ የምጫን በፍቃደኝነት ላይ የተመሰረተ፣ በክትባቱ ምክንያት የሚመጣዉን የጎንዮሽ ጉዳት በቀጥታ ለመከታተል ስራ ለይ የወለ ተክኖሎጅ ነዉ፡፡ **V-safe** በCDC የምቀርቡትን ጥያቀዎች ለመቆጣጠርና የክትባቱን ደህንነት ለመከታተል ይረዳል፡፡ እንድሁም የሁለተኛ ዙር ክትባትን ለማስታወስ እና የጎንዮሽ ጉዳትን በቀጥታ በስልክ ለመከታተል የምረዳ ነዉ፡፡ ለበለጠ መረጃ www.cdc.gov/vsafe ይጎብኙ፡፡

**ይህን Moderna COVID-19 የሚባለዉን ክትባት አለመዉሰድ ብወስንስ?**
ይህን Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት መዉሰድም አለመዉሰድም ሙብቶት ነዉ፡፡ ምንም አይነት ጫና አይደረግቦትም፡፡

**Moderna COVID-19 ከምባለዉን ክትባት ዉጭ ለCOVID-19 በሽታ መከላከያ ይኑር ይሁን?**
ለአሁን ለCOVID-19 በሽታ መከላከያ በFDA የተረጋገጠ ነገር የለም፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉን ክትባት ከሌላ ክትባት ጋር መዉሰድ ይቻላል?**
Moderna COVID-19 የምባለዉን ክትባት ከሌላ ክትባት ጋር መዉሰድ መቻል ወይም አለመቻል ለይ ምንም መረጃ የለም፡፡

**እርጉዝ ወይም ልጅ እያጠባሁ ከሆነስ?**
እርጉዝ ወይም ልጅ እያጠባሽ ከሆንሽ፣ ክትትል እያደረጉልሽ ያሉትን ሀክሞች አማክሪ፡፡

**Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት የCOVID-19 በሽታ ያመጣብኝ ይሁን?**
! ይህ ክትባት SARS-CoV-2 ስለለለዉ የ COVID-19 በሽታን አያመጣም፡፡

**የክትባት ካርዶትን በእጅዎ ይያዙ፡፡**
የመጀመርያ ዙር ክትባት ሲወስዱ ለሁለተኛ ግዜ መቼ መምጣት እንደለቦት የሚያሳይ ካርድ ይሰጦታል፡፡ ተመልሰዉ ሲመጡ ከርዱን ይዘዉ ይመጣሉ፡፡

**ለተጨማሪ መረጃ**
ጥያቄ ካሎት፣ ከዝህ በታች በተሰጠዉ  ወይም ስልክ ይጠቀሙ

በጣም ቅርብ የሆነ መረጃ ለማግኘት እባኮትን በመረጃ ወረቀቱ ላይ ያለዉን QR ኮድ እስካን ያድርጉ

| **Moderna COVID-19 ድረገጽ** | **ስልክ ቁጥር** |
|---|---|
| www.modernatx.com/covid19vaccine-eua | 1-866-MODERNA<br>(1-866-663-3762) |

## የበለጠ እንዴት ማወቅ እችላለሁ?

- ክትባቱን የምሰጡትን መጠየቅ
- CDC - https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/index.html.
- FDA - https://www.fda.gov/emergency-preparedness-and-response/mcm- legal-regulatory-and-policy-framework/emergency-use-authorization.
- በአከባብዎት የምገኙትን የህዝብ ህክምና ክፍል ያነጋግሩ፡፡

**የክትባቴ መረጃ ዬት ይመዘገባል?**
ክትባቱን የምሰጡ ሰዎች የክትባት መረጃዎትን በምትኖርበት እስተት ወይም በአከባብህ በምገኘዉ IIs ላይ ይመዘግባሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለሁለተኛ ግዜ ስመጡ ተመሳሳይ ክትባት በመጀማርያ ላይ እንደወሰዱ የሚጠቁም ነዉ፡፡ ስለ IIs የበለጠ መረጃ ለማግኘት https://www.cdc.gov/vaccines/programs/iis/about.html. ይጎብኙ፡፡

**CICP ምንድነዉ?**
CICP የፈደራል ፕሮግራም ሆኖ ይህንን ክትባት ጨምሮ ማንኛዉም አይነት ክትባት ለሚያመጣዉ የጎንዩሽ ጉዳትም ሆነ ለወጣዉ ወጭ ካሳ ለማስከፈል የሚዉል ፕሮግራም ነዉ፡፡
በአጠቃላይ ክትባቱ ከተወሰደበት ቀን ጀምሮ በአንድ አመት ዉስጥ ለ CICP ቅሬታ ርፖርት መደረግ አለበት፡፡ ለበለጠ መረጃ www.hrsa.gov/cicp/ ይጎብኙ ወይም 1-855-266-2427 ላይ ይደዉሉ፡፡

**የድንገተኛ አጠቃቀም ፈቃድ (EUA) ምንድነዉ?**
የአሜሪካ ሀገር FDA የ Moderna COVID-19 ክትባት EUA ተብሎ በሚጠራው የድንገተኛ ጊዜ ተደራሽነት ዘዴ ስር እንዲገኝ አድርጓታል ፡፡ EUA በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት የመድኃኒት እና የባዮሎጂያዊ ምርቶች ድንገተኛ አጠቃቀምን

ለማስረዳት ሁኔታዎች እንዳሉ በጤና እና በሰብአዊ አገልግሎቶች ሴክሪተሪ (HHS) መግለጫ የተደገፈ ነው ፡፡

የ COVID-19 ክትባት በ FDA ከፀደቀው ወይም ከተጣራ ምርት ጋር አንድ ዓይነት ግምገማ አልተደረገለትም ፡፡ FDA የተወሰኑ መመዘኛዎች ሲሟሉ EUA ን ሥራ ላይ ሊያውል ይችላል ይህም በቂ ፣ የተፈቀዱ ፣ ተደራሽ የሆኑ አማራጮች በሌሉበት ጊዜ ነው ፡፡ በተጨማሪም የ FDA ውሳኔ በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ምርቱ COVID-19 ን ለመከላከል ውጤታማ ሊሆን በሚችልበት አጠቃላይ የሳይንሳዊ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የምርቱ የታወቁ እና ያላቸው እምቅ ጥቅሞች ከሚታወቁ እና ሊኖሩዋቸው ከሚችሉት ጉዳቶች ሊበልጥ ይገባል፡፡ ምርቱን በ COVID-19 ወረርሽኝ ወቅት ለታካሚዎች ሕክምና እንዲውል ለማስቻል እነዚህ ሁሉ መመዘኛዎች መሟላት አለባቸው ፡፡

EUA Moderna COVID-19 የሚባለዉ ክትባት በEUA እስከምሻር ወይም እንዳይሰጥ እስከምከለከል ድረስ ለአሁን ክትባቱ COVID-19 ለማከላከል ስራ ላይ ይዉላል፡፡

©2020 ModernaTX, Inc. መብቱ የእተጠበቀ
Patent(s): www.modernatx.com/patents
የተከለሰው: 12/2020

ይህ የእውነታ ወረቀት ለኤሌክትሮኒክ የሕክምና መረጃዎች / ክትባት የመረጃሥራአት ስካን ለማድረግ ለክትባት ተቀባዮች የተሰጠ ነው ።

የባር ኮድ ቀን : 12/2020